# ይናገራል ፎቶ
## ምሕረት ዘገዬ (ከአዲስ አበባ)



**ምንጭ -**
https://www.zehabesha.com/amharic/archives/94371

“ታላላቅ ሰዎች ለምን ከትናንሽ ስፍራ?” በሚል ርዕስ መላኩ ግርማ የተባሉ ጸሐፊ ከአትላንታ ባደረሱን ጽሑፍ ላይ ከዚህ በላይ የሚገኘውን ፎቶ አየሁ፡፡ ከጽሑፉ ባልተናነሰ እንዲያውም በበለጠ ፎቶውን ደጋግሜ አነበብኩት፡፡ በመሠረቱ ፎቶን የማንበብ ሙያዊ ዕውቀት የለኝም፡፡ ነገር ግን ያገሬ ባላገር “ባናርስ እናጣምዳለን” እንደሚለው ከልምድ ብዙ መማር ይቻላልና ይህን ፎቶ በከፍተኛ ድፍረት እንደሚከተለው አነበብኩት፡፡ የስሜት ጉዳይ ነው፡፡ ስሜት ደግሞ እንደየስሜተኛው ይወሰናልና ንባቤ ትክክል ባይሆን ብዙም አትፍረዱብኝ፡፡

1. ከአቦ ለማ መገርሣ ልጀምር፡፡ ትኩረት የሰጠው ፎቶ ለመነሣቱ ይመስላል፡፡ ፈገግታውም ለፎቶ ያህል እንጅ ከልብ አይመስልም፡፡ የፎቶ ተነሽዎቹን ቅንብርና መቼቱን ወይም ድባቡን ግን ሳይወደው የቀረ አይመስልም፡፡እጆቹ ከማንም ጋር እንዳይያያዙና ያልተፈለገ የውግና ትርጉም እንዳይሰጥበት የተጠነቀቀ ይመስላል፡፡ ክራቫቱና አጠቃላይ አለባበሱ ጥንቁቅነቱን ያሳያል፡፡ የፊት ገጽታው ኮስታራነትንና ፈገግታን በአንዴ እንዲያስተናግድ ከ conscious እና subconscious የአእምሮ ክፍሎች በተመሳሳይ ቅጽበት በመታዘዙ የማይጨበጥ ፈገግታ ይታያል፡፡ ...

2. የኢትዮጵያው ኢሉሚናቲ “ሥውር” መሪያችን ጃዋር። በጣም ተደስቷል። ደስታውን ለመቆጣጠርም ትግል እያደረገ እንዳለ ይስተዋላል። ሁለቱንም መሪዎች የማቀፉ ቀጥተኛ መልእክት “የሁለቱም የበላይ አዛዥና የሥምሪት ክፍል ኃላፊ እኔ ነኝ፤ አዳሜ ዕወቂ - እነዚህ ሰዎች ከኔ ትዕዛዝ አይወጡም!” የሚል ይመስላል። ይህም መልእክት በተለይ በዕድሜ ጠገብነቱ ሳቢያ እርጅና ተጫጭኖት ላይ ላዩን እየደካከመ ውስጥ ለውስጥ ግን በልዩ መለኮታዊ ዕርዳታ እየተጠናከረ በመሄድ ላይ ለሚገኘው የአንድነቱ ጎራ “ክንዴን ተመልከቱ!” የሚል የኃይል ሚዛን ማሳያ ነው። የሽሚዙ መጨማደድ የሚጠቁመው ሥራ የበዛበት መሆኑን ነው። ፈገግታው ከልብ አይደለም - አርቲፊሻል ነው። “እኛ እንዲህ ነን!” ለማለት ያህል overact እያደረገ እንደሆነ መገመት ይቻላል።

3. አቢቹ! አቢያ ደካክሞታል። የተለመደውን አስምጥ ፈገግታውን ለማውጣት የቻለውን ሁሉ ጥረት ቢያደርግም ለዚህኛው ኹነት አልተሳካለትም። በአቢቹ ፊት የሚታየው ፈገግታ አንድን ሰው “ፈገግ በል!” ብለው በሽጉጥ እያስፈራሩት የሚያወጣው ዓይነት የለበጣ ፈገግታ ነው። ምናልባት ብዙ በመንቀሳቀሱ ከዕንቅልፍ ዕጦትና ከውጥረት የተነሣ ድካሙን መቋቋም አቅቶት ሊሆን ይችላል - አለባበሱ በተለይም የሸሚዙ መጨማደድ የሚጠቁመውም ይህንኑ ነው። ለወትሮው ከማንም ጋር ፎቶ ሲነሳ እንደሚያደርገው በዚህ ፎቶ ማንንም አላቀፈም - የሚታቀፍ ጠፍቶ ሳይሆን የፍላጎት መክዳት ሊሆን ይችላል። ያቀፈህን ማቀፍ ውለታ መመለስ ነው - አቢቹ ግን የጃዋርን ውለታ በዚህ መልክ ለመመለስ የፈቀደ አይመስልም - ጊዜውም ያን መሳይ ድራማ እንዳሁኑ በጎላ ሁኔታ የሚፈቅድ አልነበረም መሰለኝ። እንደፊቱ ንባብ እንዲያውም በዚህ ፎቶ ላይ ባይገኝ ደስታው እንደሆነ መገመት ይቻላል - በተለያዩ ምክንያት። ይህን ማለት ግን “አቢቹ ጃዋርን አይወደውም” ለማለት ሳይሆን ፎቶው ከሚኖረው ፖለቲካዊ ፋይዳ አኳያ በዚህ መልክ መፎናቀቁ (ፍቅርን ማሳየቱ) ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚያመዝን ከመገንዘብ የተነሣ ይመስላል። ብልጥ ፖለቲከኞች “የአህያ እንትን በሆድ ይያዛል” የምትባለዋን ምሣሌያዊ ብሂል ፍካሬያዊ ፍቺ በሚገባ ይጠቀሙባታል - “ሙያ በልብ” ለማለት። እንጂ ቀን ቀን ዐይጥና ድመት ሆነው ከምናያቸው ተቃራኒ ፖለቲከኞች መካከል እኮ ብዙዎቹ ማታ ማታ ባንኮኒ ላይ “ቺርስ ለጤናችን!” እያሉ ብርጭቆ ሲያጋጩ እንደሚያመሹ እንሰማለን። እነሱ ምን ይሆናሉ? ጦርነት ቢታወጅ የሚያልቀው የድሃው ልጅ፣ ኢኮኖሚው ቢናጋ የሚራብ የሚጠማው ተራው ዜጋ፣ ማኅበራዊ ቀውስ ቢፈጠር የሚጎዳው የኔ ቢጤው ተራ ሕዝብ… እነሱን ምን ነክቷቸው? እንደ አንበሣ የብረት አጥር ውስጥ በጠበንጃ ታጥረው የሚቀርብላቸውን እየበሉና እየጠጡ ይኖራሉ፤

ከእንስሳት የማይሻል ሕይወት። በአፍንጫየ ይውጣ። ሰው ከሰው ጋር ሲኖር ነው ሸጋው።

4. ዶቶር ወርቅነህ ገበየሁ። ቄንጠኛ አነሳስ ነው። ይቺ ዓይነት አነሳስ የቴክሶችን ትመስላለች። ከአገጩ የሚጀምረው ፈገግታው ወደላይ ሲያቀና ግምባሩ ላይ ሳይደርስ ያልቃል። የውሸትና የፎቶ ፈገግታ ነው። በ "ፈገግ ልበል ወይንስ አልበል" መሀል የሚመነጭ ፈገግታ ነው ፊቱ ላይ የሚነበበው። ሳይወስን ግን ፎቶው ቀደመው። አቢቹን ማቀፉ ቀረቤታውን መግለጹ ነው - ያለ ነው።

5. የሌሎቹን ማንበቡ አይጠቅምም። ንባብን ማባከን ነው። ሰላም።